MedStar Health

*ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፡- ኦክቶበር 1፣ 2009*
*ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ቀን፡- ኦክቶበር 30፣ 2023*

# *የግላዊነት ልምዶች ማስታወቂያ*
# *ለ*
# *MedStar Health, Inc.*

ይህ የግላዊነት ልማዶች ማስታወቂያ (ማስታወቂያ) ስለ እርስዎ የህክምና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና ይፋ እንደሚደረግ እንዲሁም ይህንን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎን በጥንቃቄ ይከልሱት።

## ይህን ማስታወቂያ የሚከተለው ማን ነው

ይህ ማስታወቂያ ከMedStar Health ጋር የተያያዘ ሽፋን ያለው አካልን ይመለከታል። በአሁን ጊዜ ላለ የተያያዘ ሽፋን ያለው አካል አባላት ዝርዝር፣ እባክዎን ይህንን ማስፈንጠሪያ ይጎብኙ፡- https://www.medstarhealth.org/patient-privacy-policy/hipaa-affiliated-covered-entity-designation. እንዲሁም ይህ ማስታወቂያ ከMedStar Health ጋር የተያያዘ ሽፋን ያለው አካል ውስጥ ላሉ ሁሉም የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች፣ ሰራተኞች፣ የህክምና ሰራተኞች፣ ሰልጣኞች፣ ተማሪዎች እና በጎ ፈቃደኞች ይሰራል።

## እኛ ለእርስዎ ያለን ግዴታ

MedStar Health የህክምና መረጃዎን ለመጠበቅ ቁርጠኛ ነው። ታካሚዎቻችንን ለማገልገል ባለን ተልዕኮ፣ *ሰዎችን ለመንከባከብ እና ጤናን በማሻሻል የታመነ መሪ መሆን ራዕያችን ነው።* እኛ ስለ እርስዎ መረጃን የምናዘጋጅ እንዲሁም የምናገኝ ሲሆን ጥራት ያለው እንክብካቤ ለእርስዎ ለማቅረብ እና የተወሰኑ የህግ መስፈርቶችን ለማክበር እንጠቀምበታለን። የጤና መረጃዎን ግላዊነት ለመጠበቅ እና ስለ ህጋዊ ግዴታዎቻችን፣ ግላዊ ተግባሮቻችንን እና ስለመብቶችዎ ማስታወቂያ ለእርስዎ ለመስጠት በህግ እንገደዳለን። ወቅታዊ የሆኑትን የማስታወቂያችንን ውሎች መከተል አለብን። አገልግሎት እንዲሰጡን መረጃን ለሌሎች ሰዎች እና ኩባንያዎች ስንገልጽ፣ የእርስዎን ግላዊነት እንዲጠብቁ እንጠይቃቸዋለን። ተጨማሪ ጥበቃዎችን የሚያቀርቡ ልንከተላቸው የሚገቡን ሌሎች ህጎች አሉ ለምሳሌ ከአዕምሮ ጤና፣ ከባህሪ ጤና፣ ከአልኮል እና ከሌሎች አደንዛዥ እጽን አላግባብ መጠቀም፣ ከዘረመል መረጃ እና ከተላላፊ በሽታ ወይም ከሌሎች የጤና ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ህጎች።

## የጤና መረጃን እንዴት እንደምጠቀም እና ይፋ እንደምናደርግ

**ህክምና፡-** ህክምና ወይም አገልግሎት ለመስጠት፣ የጤና እንክብካቤዎን ለማስተባበር ወይም ለማስተዳደር ወይም ለህክምና የምክር አገልግሎቶች ወይም ሪፈራል የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም እንዲሁም ይፋ ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ፣ የእርስዎን የጤና መረጃ በሃኪሞች፣ ነርሶች፣ የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ የህክምና ታዛቢዎች፣ የህክምና ተማሪዎች እና በተቋሞቻችን ውስጥ እርስዎን በመንከባከብ ከሚሳተፉ ሌሎች ሰዎች፣ በተገቢ ቁጥጥር ስር ያሉ በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ የሚሳተፉ ወይም የሚመለከቱ በስልጠና ላይ ያሉ ባለሙያዎች፣ ወይም ከተቋሞቻችን ውጭ ካሉ ሰዎች ጋር ልንጠቀም እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን። እንደ መድሃኒት ማዘዣ፣ የላብራቶሪ ስራ እና ራጅ የመሳሰሉ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማስተባበር እርስዎ የሚመለከት መረጃን ልንጠቀም ወይም ልንጋራ እንችላለን። ከኛ ተቋም ውጪ ላሉ ከሄዱ በኋላ እርስዎን በመንከባከብ ለሚሳተፉ ሰዎች ለምሳሌ ለቤተሰብ አባላት፣ ለቤት ውስጥ የጤና ድርጅቶች፣ ሃኪሞች፣ ለአረጋውያን እንክባክቤ መስጫ ቤቶች፣ ለካህናት እና ሌሎችም ሰዎች እርስዎን የሚመለከት መረጃን ይፋ ልናደርግ እንችላለን። ሪፈራል ወይም የምክር አገልግሎት ለማዘጋጀት ለጤና እቅድዎ ወይም ለሌላ አገልግሎት አቅራቢ መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023

MedStar Health

**ክፍያ፡-** ለተሰጠው ህክምና እና አገልግሎቶች ክፍያ ለመቀበል የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ከእርስዎ የመድን ኩባንያ ጋር መረጃን ልንጋራ እንችላለን ወይም ሶስተኛ ወገን የክፍያ መረጃን ለማስኬድ ይጠቀማል። ምን አይነት ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ እንደሆኑ ለማረጋገጥ፣ ለአገልግሎቶች ቅድመ ፍቃድ ለማግኘት እና ስለ ህክምናዎ እንደሚከፍሉ ለማረጋገጥ ስለ ህክምናዎ ለመንገር የመድን ኩባንያዎን ልናነጋግር እንችላለን። እርስዎን ለማስከፈል ወይም ለመክፈል ሃላፊነት ያለባቸውን ለምሳሌ በክፍያዎ የተሳተፉ የቤተሰብ አባላትን ለማስከፈል መረጃን ለሶስተኛ ወገኖች ልንገልጽ እንችላለን። የክፍያ ኩባንያዎች፣ የይገባኛል ጥያቄን የሚያሰናዱ ኩባንያዎች እና ሰብሳቢ ኩባንያዎች የመሳሰሉ ክፍያዎችን እንድናከናውን ለሚረዱን ሶስተኛ ወገኖች መረጃ ልንገልጽ እንችላለን።

**የጤና እንክብካቤ ስራዎች፡-** ህግ በሚፈቅደው መሰረት የእርስዎን የጤና መረጃ ለ MedStar Health ስራዎች ልንጠቀም እና ልንገልጽ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ተቋማችንን ለማስኬድ እና ሁሉም ታካሚዎቻችን ጥራት ያለው እንክብካቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የእርስዎን የጤና መረጃ እንደ አስፈላጊነቱ ልንጠቀም እና ልንገልጽ እንችላለን። አፈጻጸማችንን ለማሻሻል ወይም እንክብካቤ ለመስጠት የተሻሉ መንገዶችን ለማግኘት የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። ለህክምና ሰራተኞች ልዩ መብቶችን ለመስጠት ወይም የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎቻችንን ብቁነት ለመገምገም የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። ምን አይነት ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት እንዳለብን እና አዳዲስ ህክምናዎች ውጤታማ መሆን ወይም አለመሆናቸውን ለመወሰን የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም እንችላለን። ለግምገማ እና ለትምህርት አላማዎች መረጃን ለተማሪዎች፣ ባለሙያዎች እና የህክምና ታዛቢዎች ልንገልጽ እንችላለን። እንዴት እንደምንሰራ ለማነጻጸር እና የቱ ጋር ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደምንችል ለማየት የጤና መረጃችንን ከሌሎች የጤና እንክብካቤ ተቋማት ውሂብ ጋር ልናጣምር እንችላለን። ህጉን ማክበራችንን ለማረጋገጥ የጤና መረጃን ለንግድ ስራ እቅድ ልንጠቀም እንችላለን ወይም ለጠበቆች፣ የሂሳብ አማካሪዎች እና ሌሎች ልንገልጽ እንችላለን። ሌሎች መጠእንዴት እንደምንሰራ ለማነጻጸር እና የቱ ጋር ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደምንችል ለማየት እርስዎ ማን እንደሆኑ ሳያሳውቁ የጤና እንክብካቤን እና የጤና እንክብካቤ አቅርቦትን ለማጥናት የግል መረጃዎ የጠፋበትን መረጃ እንዲጠቀሙ እርስዎን የሚለይ የጤና መረጃን ልናስወግድ እንችላለን። እንደ ጤና እቅድ የምንሰራ ከሆነ፣ ለሽፋን አላማዎች የዘረመል መረጃን አንጠቀምም ወይም አንገልጽም (ይህ የረጅም ጊዜ የእንክብካቤ እቅዶችን አይመለከትም)።

**Accountable Care Organizations (ACO) እና የመድን ኩባንያዎች (ሜሪላንድ ብቻ)፡-** ለACO ወይም ለመድን ኩባንያ ክፍያ፣ ለጤና እንክብካቤ ስራዎች እና በህግ ለሚፈቀደው ሌላ አላማ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም የጤና መረጃዎን ልንገልጽ እንችላለን። ለምሳሌ፣ የታካሚ እንክብካቤን ለማሻሻል ወይም ለማስተባበር፣ ክፍያ ለማግኘት፣ የጥራት ግምገማ እና የማሻሻያ ስራዎችን ለመስራት እና ንግዶቻችንን ለማስተዳደር ከህክምና መዛግብትዎ ለመድን ኩባንያዎች መረጃን እንገልጻለን። እኢህ ለእኛ ጥያቄ በማቅረብ ለመድን አገልግሎት አቅራቢ ወይም ACO ለእንክብካቤ ማስተባበሪያ አላማ የሚገለጹ የተወሰኑ የህክምና መዝገቦችን ከማጋራት መርጠው መውጣት ይችላሉ፡- acodatasharing@medstar.net.

የግዛት ህጎች፣ ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ለመድን ኩባንያ ወይም ACO ልንገልጽ የምንችለውን የጤና መረጃ አጠቃቀም ላይ ገደቦችን ይጥላሉ። ለምሳሌ፣ በሜሪላን ግዛት ውስጥ እንክብካቤ ካገኙ፣ ለእንክባክቤ ማስተባበሪያ አላማዎች ለአንድ የመድን ኩባንያ ይፋ ማድረግን ለሽፋን ወይም ለአጠቃቀም ግምገማ አላማዎች ጥቅም ላይ ላይውል ይችላል።

**የቀጠሮ አስታዋሾች እና የአገልግሎት መረጃ፡-** የቀጠሮ ማሳሰቢያዎችን ለመስጠት ልናነጋግርዎ፣ ወይም እርስዎን ሊጠቅሙ ስለሚችሉ የህክምና አማራጮች ወይም ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ወይም ጥቅማጥቅሞችን ለእርስዎ ለማሳወቅ የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም ወይም ልንገልጽ እንችላለን።

**የስራ ተባባሪዎች**፡- በ MedStar Health ከሌሎች አቅራቢዎች ወይም አቅራቢዎች ጋር
በሚደረጉ ውሎች እንደ ስራ ተባባሪዎች የሚጠቀሱ አንዳንድ አገልግሎቶች አሉ። ለምሳሌ፣ የእርስዎን የጤና መዝገብ ቅጂዎች ስንሰራ፣ ከአማካሪዎች፣ ከሂሳብ ባለሙያዎች፣ ከጠበቃዎች፣ ከህክምና መዝገብ ባለሙያዎች እና ከሶስተኛ ወገን የሂሳብ ኩባንያዎች ጋር የቅጂ አገልግሎትን ልንጠቀም እንችላለን። በእነዚህ አገልግሎቶች ሲዋዋሉ፣ የጠየቅናቸው ስራ እንዲያከናውኑ የእርስዎን የጤና መረጃ ለተባባሪዎቻችን ልንገልጽ እንችላለን። ይሁን እንጂ የጤና መረጃዎን

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023

MedStar Health

ለመጠበቅ የስራ ተባባሪው መረጃዎን በአግባቡ እንዲጠብቅ እንጠይቃለን።

**የተወሰኑ የግብይት ተግባራት፦** የእርስዎን የህክምና መረጃ ለእርስዎ ትናንሽ ዋጋ ያላቸውን የማስተዋወቂያ ስጦታዎችን ለማስተላለፍ፣ በ MedStar Health ስለሚቀርቡ ምርቶች፣ አገልግሎቶች እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር፣ ስለ ጉዳይ አስተዳደር እና የእንክብካቤ ቅንጅት ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር እና ስለ ህክምና አማራጮች ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ልንጠቀም እንችላለን። ይህን እንድናደርግ የሚፈቅደውን ፈቃድ ካልፈረሙ በስተቀር የእርስዎን የጤና መረጃ ለማንም ሶስተኛ ወገን ለገበያ ተግባራት አንሸጥም።

**የማረሚያ ተቋማት፦** የማረሚያ ተቋም እስረኛ ከሆኑ ወይም በህግ አስከባሪ ባለስልጣን ቁጥጥር ስር ከሆኑ፣ የጤና መረጃዎን ለማረሚያ ተቋሙ ወይም ለህግ አስከባሪ ባለስልጣን ልንሰጥ እንችላለን። የእርስዎን የጤና መረጃ ለእርስዎ ጤና እና ደህንነት፣ ለሌሎች ጤና እና ደህንነት ወይም ለማረሚያ ተቋሙ ደህንነት እና ጥበቃ ልንሰጥ እንችላለን።

**የገንዘብ ማሰባሰብ ተግባራት**፦ የጤና እንክብካቤ ተልዕኮቻችንን ለመደገፍ በበጎ አድራጎት ተነሳሽነት ላይ በሰፊው እንተማመናለን። ለፕሮግራሞቻችን ለመለገስ እድል ለመስጠት፣ እርስዎን ለማግኘት የእንክብካቤ ያገኙበትን ቀን፣ የታከሙበት ክፍል ስም እና ያከምዎትን ሃኪም ስም ጨምሮ የእርስዎን ስም እና ሌሎች ውስን መረጃዎችን ልንጠቀም እንችላለን። የገንዘብ ማሰባሰብ ተግባሮቻችንን ለማስተባበር የጆርጅታውን ዩንቨርሲቲን ጨምሮ ከሶስተኛ ጋር ልንተባበር እንችላለን። እኛ ወይም ማናቸውም የእኛ ወኪሎች ለገንዘብ ማሰባሰቢያ ወይም ለበጎ አድራጎት አላማዎች ካነጋገርንዎ፣ ለወደፊት ግንኙነት እንዴት መርጠው መውጣት እንደሚችሉ ይነግሩዎታል።

**የጤና መረጃ ልውውጦች፦** ለእርስዎ ህክምና፣ ክፍያ ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ ስራዎች አላማዎች ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ የጤና መረጃዎን በተለያዩ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ወይም ሌሎች የጤና እንክብካቤ አካላት መካከል የሚለዋወጡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በጤና መረጃ ልውውጦች (HIEs) ውስጥ ልንሳተፍ እንችላለን። ለህክምና፣ ለክፍያ፣ ለጤና እንክብካቤ ስራዎች ወይም ለምርምር አላማዎች እርስዎ በሚመለከት መረጃ በHIEs አማካኝነት ልንጋራ እንችላለን። ይህ ማለት እያንዳንዳችን የተሻለ ህክምና ማቅረብ እና እንክብካቤን ማስተባበር እንድንችል ስለ እርስዎ ያገኘነውን ወይም ያዘጋጀነውን መረጃ ለውጭ አካላት (እንደ ሆስፒታል፣ የሃኪሞች ቢሮዎች፣ መድሃኒት ቤቶች፣ ወይም የመድን ኩባንያዎች) ልንጋራ እንችላለን ወይም እነሱ ስለ እርስዎ ያዘጋጁትን ወይም የሚያገኙትን መረጃ (እንደ የህክምና ታሪክ፣ የምርመራ ታሪክ ወይም የመድን መረጃ) ልናገኝ እችላለን ማለት ነው ። በተጨማሪም፣ የትኛውንም የ MedStar Health ተቋም ከጎበኙ፣ የጤና መረጃዎ እርስዎን ለመንከባከብ፣ የጤና አገልግሎቶችዎን ለማስተባበር ወይም ለሌላ ለተፈቀዱ አላማዎች ሊጠቀሙበት ለሚችሉ ሌሎች ሃኪሞች እና ሰራተኞች ሊቀርቡ ይችላሉ።

የቼሳፔክ ክልላዊ የመረጃ ስርዐት ለታካሚዎቻችን (CRISP) የምንሳተፍበት ሜሪላንድን እና ዲሲን የሚያገለግል ክልላዊ HIE ነው። በCRISP አማካኝነት ከሚገኘው የጤና መረጃዎ ወደ 1-877-952-7477 በመደወል ወይ፣ ለ CRISP መርጦ የመውጣት ቅጽ ሞልተው በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በድረገጻቸው በ www.crisphealth.org በማስገባት "መርጠው መውጣት" እና ከስራ ውጪ ማድረግ ይችላሉ። ከCRISP መርጠው ቢወጡ እንኳን፣ የህዝብ ጤና ሪፖርት እና ቁጥጥር የተደረገባቸው የአደገኛ እጾች መረጃ፣ እንደ ግዛት በሃኪም የታዘዘ መድሃኒት ቁጥጥር ፕሮግራም (PDMP) አካል፣ አሁንም ህግ በሚፈቅደው መሰረት በCRISP አማካኝነት ለአቅራቢዎች የሚቀርብ ይሆናል።

እንዲሁም እንክብካቤ ማስተባበርን እና የጤና ውጤቶችን ማሻሻልን አላማ በማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ የጤና ውሂብን ማጋራትን ለማቀላጠፍ በተጣጣመው ብሄራዊ የድርጅቶች አውታረመረብ፣ CommonWell Health Alliance® አገልግሎቶች (CommonWell) እንሳተፋለን። በCommonWell አማካኝነት ከሚገኘው የጤና መረጃዎ መርጦ የመውጣት ቅጽን ሞልተው በፖስታ፣ በፋክስ፣ በኢሜይል በማስገባት "መርጠው መውጣት" እና ከስራ ውጪ ማድረግ ይችላሉ ወይም መርጦ የመውጣት ቅጽ እዚህ ማግኘት ይቻላል፦ https://www.medstarhealth.org/patient-privacy-policy/commonwell

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023

MedStar Health

**በእንክብካቤዎ ወይም ለእንክብካቤዎ በክፍያ ላይ የተሳተፉ ግለሰቦች፦** የእርስዎን የጤና መረጃ እንዳንሰጥ ካልጠየቁን በስተቀር በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች ለምሳሌ የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች ልንሰጥ እንችላለን። ለእንክባክቤዎ ክፍያ ለሚረዳ ሰው የእርስዎን መረጃ ልንሰጥ እንችላለን። እርስዎን፣ ቤተሰብዎን ወይም ጓደኞችዎን ለአደጋ ጊዜ እርዳታ ጥረቶችን ለማቀናጀት እርስዎን ማነጋገር እንዲችሉ መረጃዎን ከሌሎች የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች፣ የመንግስት ተወካዮች ወይም የአደጋ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፣ ለምሳሌ ቀይ መስቀል፣ በድንገተኛ አደጋ ወይም በአደጋ ጊዜ እርዳታ ልናጋራ እንችላለን።

**የአካል ክፍል እና የህብረ ህዋስ ልገሳ እና የንቅለ ተከላ ተግባራት፦** እነዚህን ተግባራት ለማመቻቸት እንደ አስፈላጊነቱ የጤና መረጃዎን ከአካል ክፍል ልገሳ፣ ከአይን ወይም ከህብረ ህዋስ ንቅለ ተከላዎች ወይም ከአካል ክፍል ልገሳ ባንኮች ጋር በተገናኘ ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጽ እንችላለን።

**የታካሚ ማውጫዎች፦** በስም ለሚጠይቅዎ ለማንኛውም ሰው ለመስጠት ስምዎን፣ በተቋሙ ውስጥ የሚገኝ ቦታ እና አጠቃላይ ሁኔታዎን በማውጫው ውስጥ ልናስቀምጥ እንችላለን። ይህን መረጃ እና የእርስዎን የሃይማኖት አባልነት ስምዎን ባያውቁትም እንኳን ለካህናት ልንሰጥ እንችላለን። መረጃዎን ከማውጫው ውጪ እንድናስቀምጠው ሊጠይቁን ይችላሉ ነገር ግን ይህን ካደረጉ ጎብኚዎች እና የአበባ ሻጮች በእኛ ተቋም ውስጥ ያሉበትን ቦታ ማግኘት እንደማይችሉ ማወቅ አለብዎት። መረጃዎን ከማውጫው ውስጥ እንድናስቀምጠው ቢጠይቁን እንኳን፣ ለአደጋ ጊዜ እርዳታ ጥረቶች ወይም በታወጁ ድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ የእርስዎን መረጃ ልንጋራ እንችላለን፦

**የህዝብ ጤና ተግባራት፦** የእርስዎን የጤና መረጃ ለህዝብ ጤና ወይም ይፋዊ ተግባራቸው በሽታን፣ ጉዳትን ወይም የአካል ጉዳትን መከላከል ወይም መቆጣጠርን ለሚያካትት ህጋዊ ባለስልጣናት ልንገልጽ እንችላለን። ለምሳሌ ስለ ልደት፣ ሞት እና ስለተለያዩ በሽታዎች አንዳንድ መረጃዎችን ለመንግስት ድርጅቶች ማሳወቅ አለብን። ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ የጤና መረጃን አሟሟትን ለሚያጠኑ ሹሞች፣ ለህክምና መርማሪዎች እና ለቀብር አስፈጻሚዎች ልንሰጥ እንችላለን። የመድሃኒቶችን ምላሾች፣ በምርቶች ላይ ያሉ ችግሮችን ሪፖርት ለማድረግ ወይም የሚጠቀሙባቸውን ምርቶች እንዲመልሱ ለሰዎች ለማሳወቅ የጤና መረጃን ልንጠቀም ወይም ልንገልጽ እንችላለን። ለበሽታ የተጋለጠ ወይም በበሽታ የመያዝ ወይም የማሰራጨት ስጋት ላይ ያለን ሰው ለማሳወቅ የጤና መረጃን ልንጠቀም ወይም ልንገልጽ እንችላለን።

**በህግ፣ በህጋዊ ሂደቶች፣ በጤና ቁጥጥር ተግባራት እና በህግ አስፈጻሚዎች የሚጠየቅ፦** በፌደራል፣ በክልል እና በሌላ ህግ ስንጠየቅ የእርስዎን የጤና መረጃ እንሰጣለን። ለምሳሌ፣ የበደል፣ የቸልተኝነት ወይም የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎችን፣ እንዲሁም የተኩስ እና ሌሎች ቁስሎች ያሉባቸውን ታካሚዎች ሪፖርት እንድናደርግ ልንጠየቅ እንችላለን። እንደ መጥሪያ፣ የግኝት ጥያቄ፣ ማዘዣ፣ የክስ መጥሪያዎች ወይም ሌላ ህጋዊ ሂደት ባሉ ህጋዊ ወይም አስተዳደራዊ የችሎት ሂደቶች በምንታዘዝበት ጊዜ የእርስዎን የጤና መረጃ እንሰጣለን። ተጠርጣሪዎችን፣ የሸሹትን፣ ምስክሮችን፣ የወንጀል ሰለባዎችን ወይም የጠፉ ሰዎችን ለመለየት ወይም ለማግኘት ለህግ አስከባሪ አካል የጤና መረጃን ልንሰጥ እንችላለን። የወንጀል ድርጊት ውጤት ሊሆን ይችላል ብለን ስለምናምንበት ሞት ወይም በተቋማችን ስለተከሰተው የወንጀል ድርጊት የጤና መረጃን ለህግ አስከባሪ ባለስልጣን ልንሰጥ እንችላለን። እንደ ኦዲት፣ ምርመራዎች፣ ፍተሻዎች እና ፍቃድ ላሉ በህግ ለተፈቀዱ ተግባራት የጤና መረጃን ለጤና ቁጥጥር ድርጅት ልንሰጥ እንችላለን።

**ምርምር፦** የምርምር ፕሮፖዛሉን በገመገሙ እና የእርስዎን የጤና መረጃ ግላዊነት ለመጠበቅ መስፈርቶችን ባወጡ ህጋዊ የምርምር ግምገማ ቦርዶቻችን መካከል በአንዱ ለተፈቀደው ምርምር የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጽ እንችላለን። የጤና መረጃዎን የምርምር ፕሮጀክት ለማካሄድ ለሚዘጋጀው የMedStar Health ተመራማሪ ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጽ እንችላለን።

**ለጤና እና ለደህንነት ከባድ ስጋት፦** በጤናዎ እና ደህንነትዎ ላይ ወይም በህዝብ ወይም በሌላ ሰው ጤና እና ደህንነት ላይ የሚደርስ ከባድ ስጋትን ለመከላከል የጤና መረጃዎን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጽ እንችላለን። እንደ ህግ አስከባሪ ወይም የመንግስት ባለስልጣናት ያሉ ስጋቶችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ለማገዝ ምክንያታዊ ለሆነ ሰው የጤና መረጃን እንገልጻለን።

**ልዩ የመንግስት ተግባራት፦** በወትድርና ውስጥ ወይም አርበኛ ከሆኑ፣ በአዛዥ ባለስልጣናት በሚጠይቁት መሰረት

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023

MedStar Health

የእርስዎን የጤና መረጃ እንሰጣለን። የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚደንትን መጠበቅ ወይም የተፈቀደ የመረጃ ስራዎችን መፈጸም ለመሳሰሉ ብሄራዊ የደህንነት አላማዎች የጤና መረጃን ፈቃ ላላቸው የፌደራል ባለስልጣናት ልንገልጽ እንችላለን። ለውጭ አገልግሎት የህክምና ብቃት ውሳኔዎችን ለማድረግ የጤና መረጃን ልንገልጽ እንችላለን።

**የሰራተኞች ማካካሻ፡-** በሚመለከታቸው የሰራተኞች የማካካሻ ህጎች እና ተመሳሳይ መስፈርቶች በሚጠይቁት መሰረት የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም ወይም ልንገልጽ እንችላለን።

**የእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ**፡- በዚህ ማስታወቂያ ያልተሸፈኑ ሌሎች የጤና መረጃዎችዎ ወይም እኛን የሚገዙን ህጎች ሌሎች አጠቃቀሞች እና መግለጫዎች የሚደረጉት በእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ብቻ ነው። እነዚህ የጤና መረጃዎን መሸጥ፣ የጤና መረጃዎን ለግብይት አላማዎች መጠቀም እና የተወሰኑ የስነ አዕምሮ ህክምና ማስታወሻዎችን ይፋ ማድረግን ያካትታሉ። ፈቃድዎን በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ መሻር ይችላሉ፣ እንዲሁም በፈቃድዎ ለተሸፈኑት ምክንያቶች ወደፊት የጤና መረጃዎን መጠቀምን እና ይፋ ማድረግን እናቋርጣለን። በእርስዎ ፍቃድ የተደረጉ ማናቸውንም ይፋዊ መግለጫዎችን መመለስ አንችልም እንዲሁም ለእርስዎ ያቀረብነውን የእንክብካቤ መዝገቦች መያዝ አለብን።

## <u>የእርስዎን የጤና መረጃ በተመለከተ የእርስዎ የግላዊነት መብቶች</u>

የህክምና መረጃዎ መዝገቦች የMedStar Health ንብረት ናቸው። ይሁን እንጂ ስለ እርስዎ የምንይዘውን የህክምና መረጃ በተመለከተ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡-

**የጤና መረጃዎን የማግኘት፣ የመገምገም እና ቅጂ የመቀበል መብት**
የህክምና እና የሂሳብ መዝገቦችዎን እና ሌሎች ስለ እርስዎ ያለንን የጤና መረጃ ከአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ጋር የማግኘት፣ የመገምገም እና ቅጂ የመቀበል መብት አለብዎት። ይህንን ለማድረግ፣ እባክዎ ህክምና የተቀበሉበትን የ MedStar Health ተቋም ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የMedStar Health የግላዊነት ቢሮ ያነጋግሩ። ጥያቄዎን በጽሁፍ ማስገባት ይጠበቅብዎታል።

የጤና መረጃዎን በኤሌክትሮኒክ ወይም በወረቀት ቅጂ ለማየት ወይም ለመቀበል ሊጠይቁ ይችላሉ። እንዲሁም የመዝገቦችዎን ቅጂ በጥያቄዎ ውስጥ ለገለጸው ሰው በቀጥታ እንድንልክ ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህንን እንዴት እንደምናደርግ ይጠይቁን። ህግ በሚፈቅደው መሰረት፣ የእርስዎን መዝገብ ለመቅዳት ወይም ለመላክ የወጣውን ወጪ (እንዲሁም ጥያቄው በተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ላይ ያለውን መረጃ እንዲሰጥ ከሆነ የኤሊትሮኒክ ሚዲያ ወጪን) መሰረት ያደረገ ክፍያ ልናስከፍልዎት እንችላለን።

የህክምና መዝገብዎን ቅጂ አብዛኛውን ጊዜ በ30 ቀናት ውስጥ እናቀርባለን። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ጥያቄዎን ላንቀበል እንችላለን። ካልተቀበልን፣ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት በጽሁፍ እንነግርዎታለን እንዲሁም ውድቅ መደረጉ እንዴት እንደሚገመገም እንገልጻለን።

**የህክምና መዝገብዎን የማዘመን መብት**
ከህክምና መዝገብዎ ውስጥ አስፈላጊ መረጃ ይጎድላል ብለው ካመኑ፣ በመዝገብዎ ላይ ማሻሻያ እንድንጨምር የመጠየቅ መብት አለዎት። ጥያቄዎ በጽሁፍ መሆን አለበት እንዲሁም የጥያቄዎን ምክንያት መያዝ አለበት። ጥያቄዎን ለማስገባት፣ እባክዎ ህክምና የተቀበሉበትን ተቋም ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮ ያነጋግሩ። አብዛኛውን ጊዜ ጥያቄዎን በ60 ቀናት ውስጥ ለማሟላት ሁሉንም ጥረት እናደርጋለን። የሚሻሻለው መረጃ በእኛ ካልተዘጋጀ፣ መረጃው ትክክለኛ እና የተሟላ ነው ብለን ካመንን ወይም መረጃው ለመገምገም እና ለመቅዳት በህግ በተፈቀደልዎት መዛግብት ውስጥ ካልያዘ መዝገብዎን ለማሻሻል ያቀረቡትን ጥያቄ ላንቀበል እንችላለን። ጥያቄዎን ካልተቀበልን፣ በ60 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቂያ ይደርስዎታል።

**ይፋ ያደረግናቸውን መግለጫዎች ዝርዝር የማግኘት መብት**
ከጥያቄዎ ቀን በፊት ባሉት ስድስት አመታት ውስጥ ይፋ ያደረግናቸውን የጤና መረጃዎን ዝርዝር (ማለትም፣ የሂሳብ አያያዝ) የመጠየቅ መብት አለብዎት። ይህ ዝርዝር ለህክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ስራዎች የተደረጉ ይፋዊ

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023

MedStar Health

መግለጫዎችን እና ሌሎች የተወሰኑ የመግለጫ ልዩ ሁኔታዎችን እንዲያካትት አይገደድም። ጥያቄዎ በጽሁፍ መሆን አለበት እንዲሁም ዝርዝሩን በምን አይነት መልኩ እንደሚፈልጉ ያመልክቱ (ለምሳሌ በወረቀት፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ)። የመለጫዎችን ዝርዝር ለመጠየቅ፣ እባክዎ ህክምና የተቀበሉትን ተቋም ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮ ያነጋግሩ። በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የጠየቁት የመጀመሪያ ዝርዝር ነጻ ነው። ለተጨማሪ ዝርዝሮች፣ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ክፍያ ልናስከፍል እንችላለን።

**ለተወሰኑ አጠቃቀሞች ወይም ይፋዊ መግለጫዎች ገደብ የመጠየቅ መብት**

የህክምና መረጃዎችን ለህክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ስራዎች፣ እና በእርስዎ እንክብካቤ ወይም የእንክብካቤዎ ክፍያ ላይ ለተሳተፉ በእርስዎ ለሚታወቁ የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች የምንጠቀምበት እና የምንገልጽበት መንገድ ላይ ገደብ የመጠየቅ መብት አልዎት። ጥያቄዎ በጽሁፍ መሆን አለበት፣ እንዲሁም (1) እርስዎ መገደብ የሚፈልጉትን ልዩ መረጃ፣ (2)አጠቃቀማችንን፣ ይፋ ማድረግን ወይም ሁለቱንም መገደብ ይፈልጉ እነሆነ እና (3) ገደቦቹ ለማን እንዲተገበሩ እንደሚፈልጉ መግለጽ አለበት። በአጠቃላይ፣ በጥያቄዎ መስማማት አይጠበቅብንም፣ እና መስማማት ካልቻልን እናሳውቅዎታለን። ይሁን እንጂ፣ ጥያቄዎ የመረጃዎ ገለጻ እርስዎን እና የጤና እቅድን፣ ወይም እርስዎን የሚወክል ሌላ ሰውን የሚመለከት ከሆነ ወይም በሙሉ ህክምና ወይም አገልግሎቶች በራስዎ ወጪ የሚከፈል ከሆነ በጥያቄዎ መስማማት አለብን።

**የህግ ጥሰት ማስታወቂያ የማግኘት መብት**

የጤና መረጃዎን ህግ መጣስ ካለ የማወቅ መብት አለዎት። የህግ ጥሰት ማለት በህግ ባልተፈቀ መንገድ የጤና መረጃን ማግኘት፣ መድረስ፣ ጥቅም ላይ መዋል ወይም ይፋ ማድረግ ሲሆን ይህም ለአደጋ እንዲጋለጥ ያደርጋል።

**የታካሚ ተወካይን የመምረጥ መብት**

አንድ ተወካይ እርስዎን ወክሎ እንዲሰራ የመምረጥ መብት አለዎት። ለአንድ ሰው የህክምና ስልጣን ከሰጡ፣ ያ ሰው የእርስዎን መብቶች መጠቀም እና ስለ ጤና መረጃዎ ምርጫ ማድረግ ይችላል። እርስዎ የሰየሙት ሰው ይህ ስልጣን እንዳለው ለማረጋገጥ እና ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ለእርስዎ እንዲሰራ ጥረቶችን እናደርጋለን።

**ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች፣ የወላጆች እና የአሳዳጊዎች መብቶች**

ይህ ማስታወቂያ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችንም ይመለከታል። ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ለህክምና መረጃቸው ተመሳሳይ የግላዊነት ጥበቃዎችን የማግኘት መብት አላቸው። ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ ነጻ ከወጣ ወይም ያለ ወላጅ ወይም አሳዳጊ እውቀት ወይም ፍቃድ በሚመለከተው ህግ መሰረት ገለልተኛ የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎችን ማረግ ከቻለ፣ ለአካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ያሉትን ገለልተኛ የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎች በተመለከተ ሁሉንም የግላዊነት መብቶችን የማግኘት ስልጣን አለው።

በሚመለከተው ህግ መሰረት ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ሌላ በወላጅ ምትክ የሚሰራ ሰው ነጻ ያልሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ የጤና እንክብካቤን በሚመለከት ውሳኔዎችን ለመወሰን ስልጣን ካለው፣ MedStar Health ይህንን ማስታወቂያ በተመለከተ ጨምሮ ያንን ሰው ለአካለ መጠን ላልደረሰው ሰው እንደ ተወካይ ሊመለከተው ይገባል።

**የጤና መረጃዎን እንዴት እንደሚቀበሉ የመምረጥ መብት**

ከእርስዎ ጋር በተወሰነ መንገድ ለምሳሌ በፖስታ ወይም በፋክስ ወይም በተወሰነ ቦታ ለምሳሌ በቤት አድራሻ ወይም በፖስታ ቢሮ ውስጥ ባለ ሳጥን መልዕክት እንድንለዋወጥ የመጠየቅ መብት አለዎት። በምክንያታዊነት በተቻለን መጠን ጥያቄዎን ለማክበር እንሞክራለን። ጥያቄዎ በጽሁፍ መሆን አለበት እንዲሁም እንዴት እና የት መገናኘት እንደሚፈልጉ መግለጽ አለበት። ጥያቄ ለማስገባት፣ እባክዎ ህክምና የተቀበሉበትን ተቋም ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮ ያነጋግሩ።

**ከእኛ ጋር ሚስጥራዊ ግንኙነት የማድረግ መብት**

በፖስታ ወይም በሰጡት ስልክ ቁጥር ካገኘንዎ፣ በተለዋጭ መንገድ ወይም በተለዋጭ ቦታ እንድናገኝዎ የመጠየቅ መብት አለዎት። ጥያቄዎ ምክንያታዊ፣ በጽሁፍ የቀረበልን እና እርስዎን ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ ማቅረብ አለበት። ጥያቄዎን ወደ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የጤና እቅዶቻችን ከመሩ፣ መረጃዎን በሙሉ ወይም በከፊል

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023

MedStar Health

ይፋ ማድረግ እንዴት አደጋ ላይ እንደሚጥልዎም ማስረዳት አለብዎት። ጥያቄዎ ከክፍያ ጋር የሚገናኝ ከሆነ፣ ክፍያዎች እንዴት እንደሚስተናገዱ መረጃ እና ከእርስዎ ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ የምንገናኝበትን አማራጭ ዘዴ ማቅረብ አለብዎት።

**የዚህን የግላዊነት ልማዶች ማስታወቂያ ቅጂ የማግኘት መብት**

ወቅታዊ የሆነውን የማስታወቂያ ቅጂ በተቋሞቻችን እና በድረ ገጾችን በ www.medstarhealth.org ላይ እንለጥፋለን። ወቅታዊ የሆነውን የማስታወቂያ ቅጂ በምዝገባ ቦታዎቻችን ወይም በጥያቄዎ መሰረት ይገኛል። ወቅታዊ የሆነውን የማስታወቂያ ቅጂ ለመጠየቅ፣ እባክዎን የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮ ያነጋግሩ ወይም ወደ (410) 772-6606 ይደውሉ።

## ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች

የግላዊነት መብትዎ ተጥሷል ብለው ካሙኑ፣ ለ MedStar Health የግላዊነት ቢሮ ወይም ለጤና እና ለሰብዐዊ አገልግሎቶች መምሪያ (እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን የእውቂያ አድራሻ ይመልከቱ) መደወል ወይም ቅሬታዎን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ። ስለ ግላዊነት ልማዶቻችን ቅሬታ ካቀረቡ በእርስዎ ላይ ምንም አይነት የበቀል እርምጃ አንወስድም።

MedStar Health, Inc.
ትኩረት፡- የግላዊነት ቢሮ
10980 Grantchester Way
Columbia, MD 21044
410-772-6606
privacyofficer@medstar.net

ወይም

የU.S. የጤና እና የሰብዐዊ አገልግሎቶች መምሪያ የሲቪል መብቶች ቢሮ
200 Independence Avenue, S.W., Washington, D.C. 20201
1-877-696-6775 (ከክፍያ ነጻ)
**www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/complaints/**

ስለዚህ ማስታወቂያ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወይም የእርስዎን የግላዊነት መብቶች ለመጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎ ህክምና የተቀበሉበትን ተቋም ወይም የ MedStar Health የግላዊነት ቢሮ ያነጋግሩ።

## በዚህ የግላዊነት ልማዶች ማስታወቂያ ላይ የተደረጉ ለውጦች

ይህን ማስታወቂያ የመቀየር መብታችን የተጠበቀ ነው። ስለ እርስዎ ያለን የህክምና መረጃ እንዲሁም ወደፊት ለሚደርሰን ማንኛውም መረጃ የተሻሻለው ማስታወቂያ ተፈጻሚ የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው። ወቅታዊ የሆነውን ማስታወቂያ ቅጂ በእያንዳንዱ የMedStar Health ተቋም እና በድረገጻችንን በ www.medstarhealth.org ላይ እንለጥፋለን። በተጨማሪም፣ በአሁኑ ጊዜ ተፈጻሚ የሆነውን የማስታወቂያ ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ እና ወዲያውኑ የማስታወቂያውን ቅጂ እንሰጥዎታለን።

*የግርጌ ማስታወሻ፡- MedStar Health, Inc. የኮሎምቢያ ዲስትሪክትን፣ ሜሪላንድን እና ቨርጂኒያ ክልልን የሚያገለግል ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የጤና እንክባከቤ ስርዐት ነው። ስርዐቱ ከበርካታ የተለያዩ የጤና እንክባካቤ አቅራቢዎች እና ሌሎች ከተለያዩ የጤና እንክብካቤ አካላት የተዋቀረ ነው። እያንዳንዱ አገልግሎት አቅራቢ ለታካሚዎች በሙያዊ መንገድ እና ተፈጻሚነት ያላቸውን ህጎች እና መመሪያዎችን በማክበር ለታካሚዎች የህክምና አገልግሎቶችን ለመስጠት የራሱ ሃላፊነት አለበት።*

©2023 MedStar Health, Inc. • 23-MH-0195.092023